በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱን የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤

በርዕሱ የተጠቀሰውን ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት የ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 22 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 8 ገጽ አባሪ በድምሩ 30 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን ልከናል። በመሆኑም በገጽ 31 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን።

ከሰላምታ ጋር !

ሰለሞን መብራቱ

የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች

ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

ሚያዝያ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመሥሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት የሂሣብ መግለጫ ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል።

ዓላማ

የዚህ ደብዳቤ ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የመሥሪያ ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱበት ለማድረግ ነው።

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን (INTOSAI/ISA) መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል።

ኦዲታችን የሚያካትተው፡ -

- ✓ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና መመርመርን፣
- ✓ የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- ✓ የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ለፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ዝግጅት አግባብነት ያላቸው መሆኑን፣ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የሂሳብ መግለጫዎቹ ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል።

የሂሳብ መግለጫዎቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል። አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል።

በመሆኑም በዚህ ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ ከመሆኑም በላይ የሂሳብ መግለጫውን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ከዚህ ጋር የተያያዙ ግድፈቶችና ስህተቶች ሁሉ ሊታወቁ የሚችሉት ይህን አስመልክቶ ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ልዩ የዝርዝር ኦዲት በጥልቀት ሲከናወን መሆኑን እንገልጻለን።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ኃላፊነት ነው።

የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥራ አመራር በ2009 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች ረቂቅ ሪፖርት ላይ ምላሽ እንዲሰጥ የካቲት 27 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር OFAG.F-02.5/5/10 በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መጋቢት 5 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር 02.1.26/205 በተጻፈ ደብዳቤ ምላሽ ሰጥቷል። በመሆኑም ለሥራ አመራሩ የተዘጋጀው የመጨረሻው ሪፖርት እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. **የወጪ ሂሳብ**

1.1. ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ ያልተረጋገጡ ወጪዎች ስለመኖራቸው፤

1.1.1. ግኝት

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም. ባወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ክፍያ መመሪያ ቁጥር 3 ቀን 2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 6 ማናቸውም የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ መረጋገጥ እንዳለበት ተመልክቷል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት ላወጣቸው ወጪዎች በጀት ስለመኖሩ በበጀት ክፍሉ በቅድሚያ የሚረጋገጥና የሚፈረም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ድምራቸው ብር 1,124,685.50 የሆኑ ወጪዎች ሲፈጸሙ በጀት ስለመኖሩ የበጀት ክፍሉ በወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ ያልተፈረመ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም አስተያየት ቢሰጥበትም የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 1 ተያይዟል)

1.1.2. ሥጋት

- ☞ ለየሂሳብ መደቦቹ (ኮዶች) የተፈቀደ በጀት ሳይኖር ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።
- ☞ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል።

1.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ለወጪው በጀት የተያዘ ለመሆኑ በቅድሚያ እንዲረጋገጥ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ቀደም ሲል በነበረው የኦዲት ግኝቶች ላይ በተደጋጋሚ አስተያየት የተሰጠበት በመሆኑ ተቀብለን አሁን ላይ በቋሚነት ይህን ሥራ በማረጋገጥ የሚያከናውኑ ባለሙያዎች የመደብን ሲሆን ለወደፊቱ እንደማይኖር ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡

1.1.5. የኦዲተር አስተያየት

ባለፉት በጀት ዓመታት እንዲሁም በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም በተመሳሳይ ወጪ ከመፈጸሙ በፊት በጀት ስለመኖሩ ሊረጋገጥ እንደሚገባ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለዚህም ትክክለኛውን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋ እንደሚገባው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ይህ ሳይሆን በድጋሚ ግኝቶቹ ሊታዩ ችለዋል፡፡ አሰራሩ የተስተካከለ ስለመሆኑ በቀጣይ ኦዲት ወቅት የሚታይ ይሆናል፡፡ ለወደፊቱ መሥሪያ ቤቱ ገንዘብ ወጪ ከመደረጉ በፊት በጀት መኖሩ የሚረጋገጥበትን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

1.2. ያለተጨባጭ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፤

1.2.1. ግኝት

ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 24/3 መሰረት ከብር 100,000.00 ድረስ የሚፈጸሙ የእቃ ግዥዎች እንዲሁም ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል በወጣውና ከታኅሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው መመሪያ መሠረት እስከ ብር 200,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ:-

1. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በብር **108,000.00** ለሚኒስቴሩ አጃቢዎች፣ ሾፌሮችና ፕሮቶኮሎች የደንብ ልብስ ግዥ ሲፈጸም ግገርው የተፈጸመው ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት ከአምባሳደር ኃ/የተ/የግ/ማህበር በብር 26,459.88 ሲሆን ነገር ግን ተጠቃሚ ሠራተኞቹ በመሩጡት ተብሎ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ከትሩ ፋሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በብር 108,000.18 በመገዛቱ በልዩነት ብር 81,540.30 ፤

2. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሶፋ እና የቡና ጠረጴዛ ከሰንሜት ኢ.ታሊ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ግዥ ሲፈጽም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ድርጅት ምናየ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብር 162,949.99 ሆኖ እያለ ያለምንም ተጨባጭ ማብራሪያ ግገርው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ሰንሜት ኢ.ታሊ በብር 194,600.00 እንዲፈጸም በመደረጉ በልዩነት ብር 31,650.00፤

በድምሩ ብር 113,190.30 መሥሪያ ቤቱ ለተጨማሪ ወጪ የተዳረገ መሆኑ ታውቋል

1.2.2. ሥጋት

ግዥዎች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትሎ የማይፈጸም ከሆነ፡-

- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል።
- የመንግሥት ገንዘብ ያለ አግባብ ሊባክንና ለግል ጥቅም ሊውል ይችላል።
- በግገር አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ሊያደርግ ይችላል።
- የመንግሥት ግገር አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ምክንያት ሊሆን ይችላል።

1.2.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

አንሰተኛ ዋጋ ያቀረቡ ድርጅቶች እያሉ ግዥው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች መገዛቱ አግባብ አይደለም። ለወደፊቱም ግዥዎች በግዥ አዋጁና መመሪያው መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.2.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት በመቀበል የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን መሠረት በማድረግ ብቻ የምንፈጽምና ክትትልና ቁጥጥር የምናደርግ ይሆናል። ከግዥ ጋር በተያያዘ የግዥ መጠየቂያ መረጃ ባለመሟላቱ፣ በተጠቀሚ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ግዥው መፈጸሙ፣ ሙያተኞች መመሪያውን በሚገባ ካለመረዳት፣ በስራ ክፍሉ የተጠናከረ የሰው ኃይል ካለመኖሩ የተፈጠረ ሲሆን በኦዲት የተሰጠውን አስተያየት በመውሰድ በቀጣይ የግዥ ክፍሉን በማጠናከርና በማሟላት ተጠያቂነትን መሰረት ባደረገ መልኩ የምንፈጽም ይሆናል።

1.2.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

በመንግሥት የዕቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት ግዥው ግልጽ እና ፍትሃዊ እንዲሆን የሚፈለገውን የዕቃዎች አይነት በመዘርዘር "Specification" በማውጣት ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸው ዕቃዎችን ሊያቀርቡ የሚችሉ ድርጅቶችን በማወዳደር አነስተኛ ዋጋ ካቀረቡት ድርጅቶች ግዥው መፈጸም ነበረበት። ስለሆነም ለወደፊቱ ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.3. <u>የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸሙ ግዥዎች</u>፤

1.3.1. <u>ግኝት</u>

ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በወጣው መመሪያ መሰረት እስከ ብር 200,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የዕቃ ግዥዎች፤

እንዲሁም እስከ ብር 150,000.00 ድረስ ለሚፈጸሙ የአገልግሎት ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በብር 170,190.05 ለፈጸመው የዕቃ እና የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥዎች በመመሪያው መሰረት እስከተቻለ ድረስ ከሶስት ድርጅቶች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰብ ሲገባው የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ ግዥውን የፈጸመ መሆኑ ታዉቋል፡፡

(ዝርዝሩ በአባሪ 2 ተያይዟል)

1.3.2. <u>*ሥጋት*</u>

- በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደርጋል፡፡
- የመንግሥት ግዢ አፈጻጸምን ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የአገሪቱን ኢኮኖሚ እድገት መደገፍ እንዳይቻልና በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል ያደርጋል፡፡

1.3.3. <u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>

ግዥዎች በግዥ አዋጅና መመሪያ መሰረት እንዲፈጸሙ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.3.4. <u>**የሥራ አመራሩ ምላሽ**</u>

የተሰጠውን አስተያየት በመቀበል ለወደፊቱ በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሰረት ብቻ የምንፈጽም መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡ የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይቀርብ ከተፈፀሙ ግዥዎች ሁለቱ የተሽከርካሪና የሞተር ሳይክል ጥገና በአስመጪ ካምፓኒ የተደረጉ ሲሆን በ2010 በጀት ሁሉም ተሽከርካሪዎች በውለታ አሸናፊ በሆነው ጋራዥ የሚጠገኑበት ሁኔታ ተመቻችቷል፡፡ ሌሎች ከአስቸኳይነታቸው በተነሳ ከአንድ አቅራቢ የተፈፀሙ በተለይ ከማስታወቂያና ህትመት ስራ ጋር በተያያዘ ግኝቱን በመመሪያነት በመውሰድ በቀጣይ በዕቅድ ቀደም ብሎ እንዲፈጸም ከአቅም

በላይ ከሆነም የመንግሥት ግዥ ኤጀንሲን በማስፈቀድ በመመሪያው መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

1.3.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ብቸኛ አስመጪዎች ናቸው ተብሎ በተሰጠው ምላሽ መሰረት ብቸኛ አስመጪዎች ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ የለም። ከዚህም በተጨማሪ ግዥዎችን አቅዶ የማይፈጸም ከሆነ የግዥ ሥርዓቱን ለመጣስ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ስለሆነም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 31 መሰረት መደበኛ ያልሆኑ የግዢ ጥያቄዎችን ለማስተናገድ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመመሪያው ላይ የተዘረዘሩትን የግዢ አፈጻጸም ሥርዓቶች ሊጠብቁ ካልቻሉ ወይም መደበኛ ያልሆነ ግዢ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁ አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ለግዥ ኤጀንሲ ቀርቦ ሲፈቀድ ብቻ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም ሚኒስቴር መሥሪያ ግዥዎችን መመሪያውን ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል።

1.4. ያለሂሣብ መደቡ የተመዘገበ ሂሳብ፤

1.4.1. ግኝት

የወጪ ሂሳቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ መሥሪያ ቤቱ ለተለያዩ አገልግሎቶች የፈጸመው ክፍያ ብር 78,548.70 በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገብ ተገኝቷል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 3 ተያይዟል)

1.4.2. ሥጋት

- ☞ የተዘጋጀዉን የሂሳብ መግለጫ ታዓማኒነት ሊያሳጣዉ ይችላል።
- ☞ የሂሳብ ኮዳቸውን ሳይጠብቁ የሚከፈሉ ወጪዎች በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገው እንዳይታይ ለመሸፈን መሆኑን ሊያመላክት ይችላል።

1.4.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለወደፊቱ የሂሳብ ምዝገባ ሲያከናውን የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትን ተከትሎ ምዝገባወን ማከናወን ይኖርበታል።

1.4.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት ተቀብለን የምናርም መሆኑን እናሳውቃለን።

1.5. ከሥራ ለለቁ ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፤

1.5.1. ግኝት

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ተራ ቁጥር 10 የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ አከፋፈል ደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ/ወጪ ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች አንዱ በጡረታ፣ በሞትና በሌሎች ምክንያት ከሥራ የለቀቁ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መውጣት እንዳለባቸው ይገልጻል። በመመሪያ መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከስራ የለቀቁ ሰራተኞች ደመወዝ ከለቀቁበት ቀን ጀምሮ እንዳልተከፈላቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ለሁለት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ ብር 2,854.17 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል። (ለዝርዝሩ አባሪ 4 ተያይዟል)

1.5.2. ሥጋት

በደመወዝ አከፋፈል ወቅት ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ሊወጣ ይችላል።

1.5.3. የማሻሻያ ሃሳብ

አለአግባብ ለሠራተኞች የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ሰራተኞች ከለቀቁ በኋላ የደመወዝ ክፍያ እንዳይፈጸም የሰው ሀብት ዳይሬክቶሬት በወቅቱ ለፋይናንስ ክፍሉ

ማሳወቅ ይኖርበታል። ሂሳብ ክፍሉም አለአግባብ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

1.5.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

በሰራ ላይ የሌሉ ሰራተኞች ያልሰሩበት ደመወዝ በተመለከተ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት ተመላሽ ለማድረግ በሕግ እንዲያዝ ተደርጓል። የሥራ ክፍሎች በ20ኛው ቀን በስራ ላይ ያሉ ሰራተኞችን እንዲያሳውቁ፣ ቋሚ ያልሆኑ ሰራተኞች ወደ ባንክ ሂሣብ በቀጥታ የሚከፈል አሰራር እንዳይኖር የሰዓት ቁጥጥር ተግባራትም በጥብቅ እንዲተገበሩ የተደረገ መሆኑን እና ከሰው ሃብት ሥ/አ/ል/ዳይሬክተር ጋር በመነጋገር በመመሪያው መሠረት አሠራሩን እያስተካከልን እንገኛለን። በመሆኑ በኦዲት አስተያየቱ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል።

1.6. ያልተከፈለ ውዝፍ የስልክ አገልግሎት ሂሳብ፤

1.6.1. ግኝት

የቢሮ ቀጥታ ስልክን፣ የነዳጅና ቅባት፣ የሞባይል ስልክና የመስተንግዶ ፍጆታን ለመወሰን ተሻሽሎ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተዘጋጀው ኖርም ቁጥር 01/2008 መሠረት የቀጥታና ለሞባይል ካርድ በየደረጃው ለሚገኙ ኃላፊዎች በተወሰነው ጣሪያ መሠረት ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ከመጋቢት 2008 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 2009 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚኒስትሩ ጽህፈት ቤቱ አማካሪ ለሞባይል ስልክ በሚገለገሉበት ቁጥር 0911-636245 ብር 45,047.47 እንዲሁም በ4ጂ.ቢ. ቀጥር 0944-703388 ብር 198,997.96 በድምሩ ለብር 244,045.43 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ክፍያ ይፈጽም ዘንድ ኢትዮ ቴሌኮም የስልክ ክፍያ ቢል ቢልክም በውዝፍ የተጠየቀው ገንዘብ እንዲከፈል ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል። (ዝርዝሩ አባሪ 5 ተያይዟል)

1.6.2. ሥጋት

- ውዝፍ ክፍያዎች በወቅቱ ተጣርተው ካልተከፈሉ የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል።
- ክፍያው ካልተፈጸመ የመሥሪያ ቤቱ የስልክ ቁጥሮቹ አገልግሎት ሊቋረጥና መሥሪያ ቤቱ አግለግሎቱን እንደገና ለማግኘት ተጨማሪ ወጪ ሊያወጣ ይችላል።

1.6.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የስልክ አገልግሎቱ ለመሥሪያ ቤቱ ለሥራ ጉዳይ መዋሉ ወይም ያለመዋሉ ተጣርቶ መሥሪያ ቤቱ መሸፈን የሚገባውን እንዲሸፍን፤ ለግል አገልግሎት የዋለውን የአገልግሎት ክፍያ ደግሞ ግለሰቡ እንዲፈጽሙ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

1.6.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ያልተከፈለ ውዝፍ የሰልክ አገልግሎት ሂሣብ በማስተካከል ከቴሌኮሚኒኬሽን የሂሣብ መጠየቂያ የመጣው ከአስራ ሶስት ወራት በኋላ በመሆኑ የተፈጠረና የስልክ ወጭዎችን በማጣራት ውሳኔ እስኪያገኝ በመሆኑ ሲሆን በሞባይልና በኢንተርኔት የቆጠረው ወጪ ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም ጋር የተያያዘና ለይቶ በስራ ላይ የዋለውንና ያልዋለውን ለመለየት የሚያስቸግር በመሆኑ የኢንተርኔት አገልግሎቱን በማቋረጥ ከቀጥታ ስልክ ወደ ካርድ ክፍያ በማዞር ወጭዎችን መቆጣጠር የሚቻልበት እርምጃ ተወስዷል።

1.6.5. የኦዲተሩ አስተያየት

በመመሪያ ለስልክ አግልግሎት እንዲውል ከተፈቀዱ ጥቅማጥቅሞች በስተቀር ለስልክ አገልግሎት በጀት የሚመደበው ለሥራ ጉዳይ ለዋሉ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ክፍያዎችን ለመፈጸም መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም በማሻሻያ ሃሳቡ በተሰጠው አስተያየት መሰረት መፈጸም እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

1.7. የመደበኛ ስልክ አጠቃቀምን በተመለከተ፤

1.7.1. ግኝት

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወርሃዊ የስልክ ክፍያ የሚፈጽመው መሥሪያ ቤቱ በባለቤትነት ለያዛቸው የስልክ ቁጥሮች መሆኑን እንዲሁም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለመደበኛ ስልክ ወርሃዊ የስልክ አጠቃቀም ጣሪያ ያወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሥራ አመራር ከጥር 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሆነ የቀጥታ/ የመደበኛ ተንቀሳቃሽ ስልክ እና የኢንተርኔት አገልግሎት አጠቃቀም የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣ ቢሆንም ወርሃዊ የስልክ ክፍያ የሚፈጸምባቸው ቁጥሮች የመሥሪያ ቤቱ ስለመሆናቸው እና ለየትኛው ክፍል/ኃላፊ የተሰጡ ለመሆኑ የሚሳይ ዝርዝር ማስረጃ ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ በመሆኑ የክፍያው አግባብነት ለማረጋገጥ አልተቻለም።

1.7.2. ሥጋት

የስልክ ክፍያ የተፈጸምባቸው ቁጥሮች የመሥሪያ ቤቱ ስለመሆናቸው እና ለየትኛው ክፍል/ኃላፊ የተሰጡ ለመሆኑ ካልታወቀ (መረጃ ካልቀረበ)፡-

- ☞ ክፍያ የተፈጸመው በሥራ አመራሩ በተወሰነው ጣሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ አይቻልም።
- ☞ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ባልሆኑ ስልክ ቁጥሮች ክፍያ ሊፈጸም ይችላል።

1.7.3. የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቱ እያንዳንዱ የመደበኛ ስልክ ቁጥር ለየትኛው ክፍል/ኃላፊ እንደተሰጠ ተገቢ ሆነ መረጃ ሊኖረው ይገባል። ለኦዲት ሥራ ሲጠየቅም ማቅረብ ይኖርበታል።

1.7.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የሥራ ክፍሉን በሰው ኃይል ለማደራጀት ረዥም ጊዜ በመውሰዱና መሥሪያ ቤቱ ወደ አዲሱ ህንጻ የገባው ሐምሌ 2008 ዓ.ም በመሆኑ የቢሮ

ማደራጀት ስራው የፈጀው ጊዜ ከሰው ኃይል እጥረት ጋር ተዳምሮ መረጃዎችን በወቅቱ ማደራጀት አልተቻለም። በአሁኑ ወቅት መረጃዎችን በማጥራት የሚዘጉ ስልኮች እንዲዘጉ በሁሉም የሥራ ክፍልና ኃላፊ ያሉ ስልኮች መረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል። ግኝቱ በትምህርትነት ተወስዶ የአሰራር ሥርዓቱን የማጠናከር ስራ ይከናወናል።

1.7.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወደ አዲሱ ቢሮ የገባው 2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ከመደረጉ ከአንድ ዓመት በፊት በመሆኑ የቢሮ ለውጥ እንደ ምክንያት ሊቀርብ አይገባም። ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን የማደራጀትም ሆነ የመጠበቅ ኃላፊነት የመሥሪያ ቤቱ በመሆኑ መረጃዎቹ ተደራጅተው አይገኙም በሚል የሚሰጥ ምላሽም አጥጋቢ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ ባለቤትነት ለሚቆጣጠራቸው የስልክ ቁጥሮች መረጃዎቹን አደራጅቶ በመያዝ ባለቤት ላልሆነባቸውን (ለማይቆጣጠራቸው) የስልክ ቁጥሮች የተከፈለ ክፍያ ካለ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ለወደፊቱም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከስልክ ጋር ተያይዘው የሚነሱ የውስጥ ቁጥጥር ክፍተቶችን ቃኝቶ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ እናሳስባለን።

1.8. <u>ተመላሽ ባልተደረጉ የሞባይል ቀፎዎችና በስልክ ቁጥሮቹ ክፍያ እየተፈጸመ የሚገኝ ስለመሆኑ፤</u>

1.8.1. <u>ግኝት</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የስልክ ክፍያ የሚፈጽመው በመስሪያ ቤቱ ላሉ ኃላፊዎችና ሰራተኞች መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

1. አቶ መኮንን ማንያዘዋል ከሐምሌ 2005 ዓ.ም ጀምሮ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተዛወሩ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም እሳቸው ሲጠቀሙበት የነበረው የሞባይል ስልክ ቁጥር 0911-204404 ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ስለመደረጉ ማስረጃ ተጠይቆ

ያልቀረበ ከመሆኑም በተጨማሪ በ2009 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ክፍያዎች ውስጥ በስልክ ቁጥሩ ብር 8,655.22፣

2. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በሚኒስቴር ደኤታ ተሹመው ሲያገለግሉ የነበሩት ክብር አቶ ታደሰ ኃይሌ ህዳር 6 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር መ/10-830/4 በተጻፈ ደብዳቤ ከህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ ከኃላፊነት የተነሱ መሆኑን የተገለጸ ቢሆንም እሳቸው ሲጠቀሙበት የነበረው የሞባይል ስልክ ቁጥር 251-911-22-53-83 ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ስለመደረጉ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ ከመሆኑም በተጨማሪ በ2009 በጀት ዓመት በናሙና ከታዩት ክፍያዎች ውስጥ በስልክ ቁጥሩ ብር 4,523.35፣

በድምሩ ብር 13,178.77 አለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል።
(ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል)

1.8.2. <u>***ሥጋት***</u>

- ☞ የሞባይል ቀፎዎቹና ቁጥሮቹ ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተመላሽ ካልተደረጉ በስልክ ቁጥሩ ለሚደረግ ማንኛውም እንቅስቃሴ መሥሪያ ቤቱ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።
- ☞ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ለአላስፈላጊ ወጪ ሊደረግ ይችላል።

1.8.3. <u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>

የሞባይል የስልክ ቀፎዎቹና ቁጥሮቹ ኃላፊዎቹ ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከተዘዋወሩ በኋላ የተፈጸመው ክፍያም ለሚኒስቴር ለመሥሪያ ቤቱ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይፈጠር ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል።

1.8.4. <u>**የሥራ አመራሩ ምላሽ**</u>

የመደበኛ ስልክ ክፍያ የተፈጸመባቸው የመሥሪያ ቤቱ ስልኮች ቀየጥሮች ለመሆናቸው፣ ለየትኛው ኃላፊና ሥራ ክፍል እንደተሰጡ እና በተቀመጠው የአፈጻጸም መመሪያ መሰረት ለመፈጸሙ የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ

ያልቻለው የሥራ ክፍሉን በሰው ኃይል ለማደራጀት ረዥም ጊዜ በመውሰዱና መሥሪያ ቤቱ ወደ አዲሱ ሕንጻ የገባው ሐምሌ 2008 ዓ.ም በመሆኑ የቢሮ ማደራጀት ሥራው የፈጀው ጊዜ ከሰው ኃይል እጥረቱ ጋር ተዳምሮ መረጃዎችን በወቅቱ ማደራጀት አልተቻለም ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን መረጃዎችን በማጥራት የሚዘጉ ስልኮች እንዲዘጉ በሁሉም የሥራ ክፍልና ኃላፊዎች ጋ የሚገኙ ስልኮች መረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል። በቀጣይ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ መመሪያውን በማሻሻል በተቀመጠው አሰራር የሚፈጸም ይሆናል። ግኝቱ በትምህርትነት ተወስዶ የአሰራር ሥርዓቱን የማጠናከር ሥራ ይከናወናል።

1.9. ከመመሪያው ውጪ የተከፈለ የቤት አበል፤

1.9.1. ግኝት

በዋና እና በምክትል ዋና ዳይሬክተር ደረጃ ተሹመው የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ለሚመሩ ኃላፊዎች የሚሰጥ ጥቅማጥቅምን በተመለከተ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ80-899/62 በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት የቤት አበል በወር 1,500.00 እንዲያገኙ ውሳኔ ተላልፏል። ሆኖም በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ የሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር ሆነዉ ለተመደቡት ኃላፊ ከመጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 1,500.00 በጠቅላላው ብር 24,000.00 የቤት አበል ተከፍሏቸዉ ተገኝቷል።

1.9.2. ሥጋት

- የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ ሊባክን ይችላል።
- መመሪያውን ተከትሎ ክፍያ ያለመፈጸም ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል።

1.9.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ከመመሪያው ውጭ የተከፈለው የቤት አበል ብር 24,000.00 ክፍያ ተመላሽ ሆኖ ለመንግስት ገቢ ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል። ለወደፊቱም ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት በመመሪያው መሰረት መሆኑን በቅድሚያ መረጋገጥ ይኖርበታል።

1.9.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ለዋና ዳይሬክተር በሹመት ለተመደቡ በሚለው መመሪያ መሰረት የተከፈለ ሲሆን መመሪያ ላይ ያለው አረዳድ መሥሪያ ቤቱ በዋና ዳይሬክተር በሹመት በሚመደብ ኃላፊ ይመራ ተብሎ ሲፈቀድ መመሪያው ላይ ይመለከታል የሚልና የሌሎች ተቋማትም በዚሁ ደረጃ ላሉ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች የሚከፈል በመሆኑ ሲሆን በኦዲት በተሰጠው አስተያየት መሰረት ሹመቱን የሰጠው የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽህፈት ቤት ማብሪሪያ የሚጤቅበት ይሆናል።

1.9.5. የኦዲተሩ አስተያየት

ግንቦት 9 ቀን 2004 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ30-894/5 የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ያወጣው መመሪያ በዋና እና በምክትል ዋና ዳይሬክተር ደረጃ ተሹመው የተለያዩ ባለበጀት የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ኃላፊዎች የሚያገኙት ጥቅማ ጥቅሞችን በተመለከተ የወጣ መመሪያ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ጥቅማ ጥቅሞቹ የተፈቀዱት በዋና እና በምክትል ዋና ዳይሬክተር ደረጃ ተሹመው የተለያዩ ባለበጀት የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ለሚመሩ ኃላፊዎች ብቻ ስለሆነ የተፈጸመው ክፍያ ተገቢነት የለውም። ስለሆነም ክፍያው ተመላሽ እንዲሆን ወይም በሚመለከተው የመንግሥት አካል እንዲፈቀድ መደረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

1.10. ተገቢው የሂሳብ ምዝገባ ማስተካከያ ያልተሰራለት እና የመጀመሪያው የሂሳብ ምዝገባ ስህተት ሳይኖረው የተሰራ የሂሳብ ማስተካከያ፤

1.10.1. ግኝት

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተከናወኑት የሒሳብ ማተካከያዎች የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ያወጣውን የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት የተከተሉ መሆኑን እንዲሁም የሂሳብ ማስተካከያዎቹን አግባብነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የመጀመሪያው የሂሳብ ምዝገባ ስህተት ሳይኖረው ለብር 2,554,478.00 ተገቢ ያልሆነ የሂሳብ ማስተካከያ ተሰርቶ ምዝገባ የተከናወነ መሆኑ ታውቋል።

(ለዝርዝሩ አባሪ 7 ተያይዟል)

1.10.2. ሥጋት

- የተሰራው ማስተካከያ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት የወጣውን በጀት ለመሸፈን ሊሆን ይችላል።
- የተዘጋጀውን የሂሳብ ሪፖርት ተዓማኒነት ሊያሳጣው ይችላል።

1.10.3. የማሻሻያ ሃሳብ

የተሰራው ማስተካከያ እንዲስተካከል፤ ለወደፊቱም የማስተካከያ ምዝገባ ከመከናወኑ በፊት ትክለኛነቱና አግባብነቱ በቅድሚያ እንዲረጋገጥ መደረግ ይኖርበታል።

1.10.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

የበጀት ኮድ ለማስተካከል ታስቦ የተሰራ ቢሆንም ስህተት መሆኑን አይተናል። ስለሆነም የሂሣብ ማስተካከያ ምዝገባ ከመስራቱ በፊት ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ የተረዳን ሲሆን አሁን ላይ ወደ ነበረበት የሂሣብ ምዝገባ ለመመለስ የበጀት አመቱ ሂሣብ ስለተዘጋና ለማስተካከል የምንቸገር በመሆኑ በኦዲተሩ የሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበልን መሆኑን እንገልጻለን።

1.10.5. የኦዲተሩ አስተያየት

በግኝቱ የተገለጸው ብር 2,554,478.00 የሂሳብ መደብ ማስተካከያ መሆኑ በሰነዱ ላይ በግልጽ ይታያል፡፡ በበጀት መደብ ላይ (BI Code) የተደረገ ማስተካከያ ቢሆን ኖሮ መጀመሪያ የተመዘገበውን ትክለኛው የሒሳብ ኮድ (መደብ) ሊቀየረው አይገባም፡፡ ሁኔታውን ለመገንዘብ እንደተቻለው የበጀት ማስተካከያ የተሰራበት ምክንያት በበጀት ዓመቱ መዝጊያ ወቅት ለሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ በብልጫ የተከፈለውን በጀት ለማስተካከል ሲባል የተሰራ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ስለሆነም መሥሪያ ቤቱ የማስተካከያ ምዝገባ ከማከናወኑ በፊት ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

2. ንብረት

2.1. ሳይጠገኑ/ሳይወገዱ ያለአገልገሎት ቆመው የሚገኙ መኪናዎች እና ያለአገልግሎት የቆመ ሞተር ሳይክልን በተመለከተ፤

2.1.1. ግኝት

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተሽከርካሪዎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ አገልግሎት መስጠት የሚችል ኮድ ኢ.አ 0652 የሆነ አንድ ሞተር ሳይክል አገልግሎት ሳይሰጥ ከአንድ አመት በላይ በንብረት ክፍል ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

2.1.2. ሥጋት

ሞተር ብስክሌቱ አገልግሎት ሳይሰጥ በቆየ ቁጥር ለብልሽት ሊዳረግ ይችላል፡፡

2.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ለአገልግሎት የቆመው ሞተር ሳይክል አገልግሎት ላይ እንዲውል መደረግ ይኖርበታል፡፡

2.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

ያለአገልግሎት የቆመው ሞተር ሳይክል በኦዲት ግኝቱ መሰረት ተስተካክሎ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል። በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

3. በጀት

3.1. ከ10% በላይ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት፤

3.1.1. ግኝት

ለሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት የመደበኛ ወጪ ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው በጀት አጠቃቀም በየሂሳብ ኮዶች ሲታይ ከ10% በላይ ብር 14,526,957.08 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ ታውቋል። (ለዝርዝሩ አባሪ 8 ተያይዟል)

3.1.2. ሥጋት

የወጪ ሂሣብ በጀቱ በዕቅዱ መሠረት አለመፈፀሙ የመሥሪያ ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል።

3.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

3.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

መሥሪያ ቤቱ በ2009 በጀት ዓመት ወደ አዲሱ ህንጻ ሲገባ ቢሮው በሚመጥነው መሰረት አስፈላጊ የሆኑ የሰው ኃይል የማሟላት፣ ለዚህ የሰው ኃይል ግብዓት ማቅረብ፣ ሌሎች ከሰው ሃይል መሟላትን ታሳቢ ያደረገ ተግባራትን ለመፈጸም ተሳቢ ተደርጎ የተያዘ ቢሆንም የሰው ኃይሉን ለማሟላት በተለይ በሲኒየር የስራ መደቦች በተደጋጋሚ ማስታወቂያ ቢያወጣም በገበያው ላይ የሰው ኃይል የሰው ኃይል ማግኘት ባለመቻሉና

በነዚህ የሰው ኃይሎች የሚፈፀሙ ተግባራት በዕቅዱ መሰረት አለመከናወናቸው ግብዓቶችን ከገበያው ማግኘት አለመቻሉ ዋና ዋና ምክንያት ሲሆን በበጀት ዓመቱ 3ኛ ሩብ ዓመት በመገምገም በቀጣይ ስራ ላይ ላይውል በሚችሉ ላይ ውሳኔ በመስጠት ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር የደመወዝ በጀት ተመላሽ ተደርጓል። በግብዓት አቅርቦት በገበያ ላይ እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ይገኛል የሚል ታሳቢ በመወሰዱ ከሌላው የሂሣብ እርዕስት መመለስ አልተቻለም። ቢሆንም ግን በሁሉም የሂሣብ እርዕስት በማየትና በማጣራት አስቀድመን ማሳወቅ እንዳለብን የተረዳንና በመሆኑ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሣብ ተቀብለን ለወደፊቱ የምናስተካክል ይሆናል።

3.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሚኒስትር መሥሪያ ቤቱ በበጀት ዕቅድ ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። በተጨማሪም መሥሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙ ላይ ክትትል በማድረግ እና የማይጠቀምበትን በጀት ለይቶ በማውጣት የበጀት እጥረት ላለባቸው መሥሪያ ቤቶች የበጀት ዝውውር ተደርጎ ጥቅም ላይ እንዲውል ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አስቀድሞ ማሳወቅ እንዳለበት ለማሳሰብ እንወዳለን።

4. <u>ልዩ ልዩ</u>

4.1. <u>እርምጃ ያልተወሰደበት የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች</u>፤

4.1.1. <u>ግኝት</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አንድ የስብሰባ ጠረጴዛ ግዥ ለመፈጸም ከሳን ጁን ፈርኒቸር ሰኔ 9 ቀን 2008 ዓ.ም በሰበሰበው የዋጋ ማቅረቢያ ቁጥር

4060 መሰረት ሻጩ፡ ድርጅት ከሽያጩ፡ ላይ 10% ቅናሽ የሚያደርግ ለመሆኑ የገለጸ ቢሆንም ሰኔ 21 ቀን 2008 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 611063 ግዥው ከድርጅቱ ሲፈጸም ክፍያው መቀነስ የሚገባው ብር 5,728.69 ሳይቀነስ ክፍያው በሙሉ የተፈጸመ መሆኑ፣

2. አቶ ሄኖክ ግዛቸው መኩሪያ ከነሐሴ 14 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከሥራ የለቀቁ በመሆኑ የ13 ቀን ደመወዝ ብር 870.13 ሊከፈል ሲገባ የሙሉ ወር ደመወዝ ብር 2,008.00 በመከፈሉ ብር 1,137.86 ያልሰሩበት ደመወዝ የተከፈለ መሆኑ፣

ተገልጸ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም፣ በዚህ በጀት ኣመት ኦዲት ወቅትም ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ በድጋሚ ተገኝቷል፡፡

4.1.2. *ሥጋት*

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡-

- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም፣ ለመንግሥት ገንዘብና ንብረት መባከን እና አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

4.1.3. የማሻሻያ ሃሳብ

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም በኦዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት ተገቢው እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

4.1.4. የሥራ አመራሩ ምላሽ

- ቀደም ሲል እንዳሳወቅነው መጋቢት 2009 ዓ.ም በደ/ቁጥር 02/1.3/586 ለሳንጃን ፈርኒቸር ደብዳቤ የተጻፈ በመሆኑ በቀጣይ ክትትልና

ቁጥጥር በማድረግ የምናስመልስ ይሆናል። የተሰጠውንም የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብለናል።

- የአቶ ሂኖክ ግዛቸው መኩሪያ ጉዳይ በህግ ክፍሉ በኩል የተያዘና በፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝቶ አድራሻቸው በመጥፋቱ ምክንያት በመሆኑ ነው።

4.1.5. <u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እርምጃ ላልተወሰደባቸው ግኝቶች ትኩረት በመስጠት ተገቢውን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት በድጋሚ ለማሳሰብ እንወዳለን።

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ስለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን።

አባሪ. 1

በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈጸመ ክፍያ ዝርዝር ፡

ተራ ቁጥር	በወጪ የተያዘበት ቀን	የሂሳብ መደብ	የወጪ ማስመሰከሪያ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	የገንዘቡ ልክ	
1	06/11/08	6232	CPV 0844596	ለትራንስፖርት ክፍያ	300	00
2	30/01/09	6258	CPV 0970453	ለስልክ ወጪ	6,000	00
3	16/02/09	6256	BPV 0819453	ለአገልግሎት ወጪ	101,720	53
4	29/02/09	6253	BPV 0819492	ለማስታወቂያ ስራ	125,161	40
5	14/03/09	6256	CPV 0970544	ለአገልግሎት ወጪ	1,500	00
6	19/03/09	6233	BPV 0819541	ለመስተንግዶ ወጪ	16,788	04
7	19/03/09	6233	BPV 0819543	ለመስተናግዶ ወጪ	10,670	68
8	06/04/09	6232	CPV 0970611	ለትራንስፖርት ክፍያ	3,004	00
9	11/04/09	6271	BPV 0819600	ለስልጠና ወጪ	11,338	40
10	03/09/09	6314	BPV 049111	ለጠረጴዛ ግዥ	171,700	01
11	03/09/09	6314	BPV 049112	ለጠረጴዛ ግዥ	132,500	01
12	03/09/09	6314	BPV 049115	ለወንበር የተገዛበት	144,000	06
13	03/09/09	6314	BPV 049115	ለጠረጴዛ ግዥ	171,700	05
14	11/09/09	6233	BPV 049134	ለመስተንግዶ ወጪ	19,059	37
15	17/09/09	6258	BPV 049143	ለስልክ ወጪ	102,664	86
16	17/09/09	6258	BPV 049144	ለስልክ ወጪ	106,385	52
	ጠቅላላ ድምር				1,124,685	50

አባሪ. 2

<u>የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ዝርዝር ፣</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የሂሳብ መደብ	የወጪ ደረሰኝ ቁጥር	የተከፈለው ድርጅት ወይም ግለሰብ ስም	የተገዛው እቃ ወይም አገልግሎት አይነት	የገንዘብ መጠን
1.	12/12/08	6253	0818309	ፋና ብሮድ ካስቲንግ ኮፕሪሽን አክሲዮን ማኅበር	ማስታወቂያ በሬድዮ የተነገረበት	9,326.50
2.	03/02/09	6241	0819424	ከኒያላ ሞተርስ አክሲዮን ማኅበር	መኪና ሰርቪስ የተደረገበት	31,850.49
3.	03/02/09	6213	0819425	ጆይ ማስታወቂያ.ድርጅት	ኢንቨስትመንት ፎረም ሲካሄድ ባነር የሰቀሉበት	8,625.00
4.	11/02/09	6233	0819442	ከአቢጊያ ደርበው ባህላዊ የገጸ በረከት	የአግሮ ኢንቨስትመንት መስተንግዶ .	66,300.00
5.	16/02/09	6241	0819454	ከሀግቤስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር	ሞተር ሳይክል የተጠገነበት	34,736.50
6.	21/02/09	6253	0819460	ፋና ብሮድ ካስቲንግ ኮፕሪሽን አክሲዮን ማኅበር	ማስታወቂያ በሬድዮ የተነገረበት	13,432.00
7.	06/09/09	6253	048925	አደይ ትናሳኤ ሚዲያና ኢንተርቴይመንት ኃላ/የተ/የግ/ማኅበር	የማስታወቂያ ሥራ	5,919.56
		ድምር				**170,190.05**

አባሪ. 3

<u>ያለሂሣብ መደቡ የተመዘገበ ሂሣብ ዝርዝር ፤</u>

ተራ ቁጥር	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	የወጪው ምክንያት	ወጪው የተመዘገበበት የሂሣብ መደብ	መመዝገብ የነበረበት የሂሣብ መደብ	የገንዘቡ ልክ
1.	24/04/09	JV 568624	**ለሚኒስቴር ዴኤታ የቢሮ ዕቃዎች ግዢ የተፈጸመ**	6313	6314	58,850.02
2.	25/08/09	BPV 049087	**የውሎ አበል ክፍያ**	6231	6232	400.00
3.	30/09/09	JV 568789	**ለክልሎች ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ኮርፖሬሽን የተዉጣጡ የኃላፊዎች ስልጠና**	6232	6271	19,298.68
ድምር						78,548.70

አባሪ .4

<u>ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ ደመወዝ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	የሠራተኛው ሥም	ከሥራ የለቀቁበት ቀን	የደመወዝ ልክ	ከስራ ከለቀቁ በኋላ ክፍያ የተፈጸመበት ጊዜ	ተከፍሎ የተገኘ	መከፈል የሚገባው	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ
1	**ወ/ሮ ዝማም ገ/ህይወት**	**13/04/2009**	**3,425.00**	**የታህሳስ ወር2009ዓ.ም የ18 ቀን ደመወዝ**	**3,425.00**	**1,370.00**	**2,055.00**
2	**አቶ ታምራት በላይ**	**24/04/2009**	**3,425.00**	**የታህሳስ ወር2009ዓ.ም የ 7 ቀን ደመወዝ**	**3,425.00**	**2,625.83**	**799.17**
ድምር					**6,850.00**	**3,995.83**	**2,854.17**

አባሪ. 5

<u>ያልተከፈለ ውዝፍ የስልክ ሂሳብ ዝርዝር ፤</u>

ስልክ ቁጥር	0944-703388	0911-636245	ድምር
ቢል የመጣበት ወር	የገንዘቡ ልክ	የገንዘቡ ልክ	
መጋቢት/2008	3,528.82	0.00	3,528.82
ሚያዚያ/2008	8,968.36	0.00	8,968.36
ግንቦት/2008	50,627.40	0.00	50,627.40
ሰኔ/2008	31,437.40	0.00	31,437.40
ሐምሌ/2008	24,292.22	1,812.68	26,104.90
ነሐሴ/2008	22,855.91	2,831.24	25,687.15
መስከረም/2009	521.74	760.83	1,282.57
ጥቅምት/2009	521.74	655.78	1,177.52
ህዳር/2009	7,851.38	1,372.47	9,223.85
ታህሣሥ/2009	4,266.97	4,818.76	9,085.73
ጥር/2009	2,109.87	2,548.30	4,658.17
የካቲት/2009	8,989.39	5,858.22	14,847.61
መጋቢት/2009	23,343.53	8,303.28	31,646.81
ሚያዚያ/2009	9,683.23	16,085.91	25,769.14
ድምር	198,997.96	45,047.47	244,045.43

አባሪ .6

ተመላሽ ያልተደረጉ የሞባይል ቀፎዎችና እንዲሁም በቁጥሮቹ የተፈጸሙ ክፍያዎችን የሚያሳይ ዝርዝር፤

የሞባይል ስልክ ቁጥር	የስልክ አገልግሎቱ የተገኘበት ወር	የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር	ወጪው የተመዘገበበት ቀን	የገንዘቡ መጠን
0911-204404	ከሀምሌ 2008 እስከ መስከረም 2009 ድረስ	0819580	30/03/2009	5,154.68
	ከጥቅምት 2009 እስከ የካቲት 2009	049033	03/08/2009	3,049.97
	መጋቢት 2009	049143	17/09/2009	450.57
	ድምር			**8,655.22**
0911-225383	ጥር 2009	049033	03/08/2009	973.97
	የካቲት 2009	049033	03/08/2009	991.22
	መጋቢት 2009	049143	17/09/2009	1,002.03
	ግንቦት 2009	049298	27/10/2009	1,556.13
	ድምር			**4,523.35**
	ጠቅላላ ድምር			**13,178.57**

<u>የመጀመሪያው የሂሳብ ምዝገባ ስህተት ሳይኖረው የተሰራ የሂሳብ ማስተካከያ ዝርዝር፤</u>

ተራ ቁጥር	ምዝገባው የተከናወነበት ቀን	የጆርናል ቫውቸር ቁጥር	የወጪው አይነት	የሂሳብ መደብ	በመሥሪያ ቤቱ የተሰራ የማስተካከያ ምዝገባ		የሂሳቡ መደብ	ወደ ቀድሞ ምዝገባ መመለስ የሚገባው የሂሳብ ማስተካከያ	
					በዴቢት	በክሬዲት		በዴቢት	በክሬዲት
1.	30/10/09	JV 568940	**የስፖርት ትጥቅ ልብስ ግዥ**	6219	4,998.00		6211	4,998.00	
				6211		4,998.00	6219		4,998.00
2.	30/10/09	JV 568940	**የሲሚንቶ ግዥ**	6219	4,930.00		6244	* 4,930.00	
				6243		4,930.00	6219		4,930.00
3.	30/10/09	JV 568940	**የህትመት ሥራ**	6271	1,444,550.00		6213	1,444,550.00	
				6213		1,444,550.00	6271		1,444,550.00
4.	30/10/09	JV 568940	**የቤት ኪራይ**	6271	1,100,000.00		6252	1,100,000.00	
				6252		1,100,000.00	6271		1,100,000
ድምር					2,554,478.00	2,554,478.00		2,554,478.00	2,554,478.00

* ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለትን ሂሳብ የሚያመለክት ነው፡፡

ከ10% በላይ ያልተሰራበት የመደበኛ በጀት ዝርዝር፤

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
የበጀት ኮድ 244/01/01				
6116	1,080.00	0.00	1,080.00	100
6131	1,883,960.00	867,137.86	1,016,822.14	54
6212	824,120.00	676,823.79	147,296.21	18
6215	330,040.00	198,409.52	131,630.48	40
6218	500,000.00	426,222.74	73,777.26	15
6219	176,800.00	123,576.33	53,223.67	30
6231	3,750,400.00	1,425,551.71	2,324,848.29	62
6232	1,951,170.00	1,561,452.61	389,717.39	20
6233	7,025,400.00	6,141,903.88	883,496.12	13
6244	144,000.00	44,826.44	99,173.56	69
6251	1,000.00	0.00	1,000.00	100
6252	3,220,000.00	2,757,333.66	462,666.34	14
6253	2,268,000.00	1,460,870.62	807,129.38	36
6254	835,390.00	422,370.29	413,019.71	49
6256	1,800,000.00	456,626.59	1,343,373.41	75
6257	212,000.00	155,587.70	56,412.30	27
6258	2,244,500.00	1,895,560.20	348,939.80	16
6259	165,000.00	134,555.73	30,444.27	18
6271	2,282,530.00	772,047.34	1,510,482.66	66
6419	1,419,866.11	161,436.34	1,258,429.77	89
የበጀት ኮድ 244/02/01				
6131	296,730.00	247,538.70	49,191.30	17
6212	270,480.00	157,119.74	113,360.26	42
6213	795,000.00	425,501.33	369,498.67	46
6231	1,735,150.00	491,104.08	1,244,045.92	72

የወጪ ሒሳብ መደብ	የተፈቀደ በጀት	በሥራ ላይ የዋለ በጀት	ያልተሰራበት በጀት	
			የገንዘቡ መጠን	በፐርሰንት (%)
6232	1,004,400.00	839,814.90	164,585.10	16
6251	20,000.00	0.00	20,000.00	100
6271	321,500.00	134,964.24	186,535.76	58
6313	447,000.00	358,509.97	88,490.03	20
የበጀት ኮድ	**244/03/01**			
6212	80,060.00	37,608.80	42,451.20	53
6231	189,870.00	16,937.60	172,932.40	91
6232	269,970.00	221,756.00	48,214.00	18
6233	501,200.00	232,832.12	268,367.88	54
6271	240,000.00	8,150.00	231,850.00	97
6313	262,490.00	88,018.20	174,471.80	66
ድምር	**37,469,106.11**	**22,942,149.03**	**14,526,957.08**	

<u>በሥራ አመራር ሪፖርት በተጠቀሱት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር</u>

የኦዲት ተደራጊ መሥሪያ ቤት ስም:- ___________________________

ኦዲት የተደረገው ሂሳብ በጀት ዓመት:- ___________________________

የተዘጋጀበት ቀን፡ - ___________________

ተራ ቁጥር	የኦዲት ግኝቶች	የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች	እስከአሁን የተወሰዱ ማስተካከያ እርምጃዎች	ቀሪ ማሻሻያ ሃሳቦች ተግባራዊ የሚደረጉበት ጊዜ	ኃላፊነት የተሰጠው የሥራ ክፍል	ምርመራ

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ይህ መርዓ-ግብር እና የኦዲት ሪፖርቱ ለመ/ቤትዎ እንደደረሰ የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ ተሞልቶ በ7 ቀናት ውስጥ ለመ/ቤታችን ካልተመለሰ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በምናቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ “ለኦዲት ሪፖርት ማሻሻያ ሃሳቦች አተገባበር መርዓ-ግብር መልስ ያልላኩ መሥሪያ ቤቶች” ዝርዝር ውስጥ እና እርምጃ አለመወሰዱ ተጠቅሶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚቀርብ መሆኑን እንገልፃለን።